ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከሚያዚያ 25- ግንቦት 3ቀን 2017 ዓ.ም
MAY 3 - 10, 2026 G.C

1. የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለስጋ ምርት የወጪ ንግድ እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው- የኢትዮጵያ ስጋ አምራችና ላኪዎች ማህበር

ኢዜአ፡ ግንቦት 2/2018

በኢትዮጵያ የተደረገው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለስጋ ምርት የወጪ ንግድ እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን የኢትዮጵያ ስጋ አምራችና ላኪዎች ማህበር ገለፀ።

የኢትዮጵያ ስጋ አምራችና ላኪዎች ማህበር ፕሬዝዳንት ከሊፋ ሁሴን እንዳሉት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ በውጭ ምንዛሬ የተደረገው ማሻሻያ በዘርፉ ላይ ትልቅ እመርታ አምጥቷል።

ዘርፉ በህገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ሲጎዳና ከውጭ ምንዛሬ ጋር በተያያዘ በስጋ መዳረሻ ገበያ የተወዳዳሪነት ችግር እንደነበረበት አውስተዋል።

የኢኮኖሚ ሪፎርሙ በአቅርቦትና በመዳረሻ ገበያ የነበረውን ችግር መፍታቱን አመልክተው፤ ወደ ውጭ የሚላክ የስጋ ምርት በመጠንና በገቢ በከፍተኛ ደረጃ ማደጉንም ገልጸዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት ስምንት ወራት ብቻ 87 ሚሊዮን ዶላር ከስጋ ወጪ ንግድ መገኘቱን ገልፀው፤ የእስካሁኑ አፈፃፀም ከአምና በጀት ዓመት የተሻለ የወጪ ንግድ ገቢ እንደሚገኝ አመላካች መሆኑን ተናግረዋል።

የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የስጋ ምርት መዳረሻ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በዋነኛነት ሳዑዲ አረቢያና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ እንዲሁም ሌሎች የአካባቢው ሀገራት እየተላከ መሆኑን ገልጸዋል።

የስጋ ተረፈ ምርት ወደ ቬትናምና ሆንግ ኮንግ እንደሚላክ ጠቅሰው፤ የአፍሪካ አህጉር አቀፍ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን ተከትሎ ወደ ጋና እና ሶማሊያ ምርት እየተላከ እንደሆነም አስረድተዋል።

የአፍሪካ አህጉር አቀፍ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን መሠረት በማድረግም የመዳረሻ ገበያን ለማስፋት እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8812206

2. የኢትዮጵያ አምራቾች ከማምረት ባሻገር የአፍሪካ ገበያን መጠቀም የሚያስችል የንግድ ትስስር መፍጠር አለባቸው

ኢዜአ፡ ሚያዝያ 25/2018

የኢትዮጵያ አምራቾች ከማምረት ባለፈ የአፍሪካን ገበያ መጠቀም የሚያስችል የንግድ ትስስር መፍጠር እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስገነዘቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሚያዝያ 25 እስከ 30 ቀን 2018 ዓ.ም የሚቆየውን የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ኤክስፖ መርቀው ከፍተዋል።

ለአራተኛ ጊዜ "ኢትዮጵያ ታምርት ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት" በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል በተዘጋጀው ኤክስፖ ላይ፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ቴዎድሮስ ምሳረት፣ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊና የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበልን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዚህ ወቅት እንደተናገሩት፤ ባለፉት አራት ዓመታት በውጭ ምንዛሬ ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ረገድ ከፍተኛ ስኬት ተመዝግቧል።

አምራቾችና የኢንዱስትሪ ዘርፍ ተዋንያን የኢኮኖሚ አርበኝነትን ሊላበሱ እንደሚገባ የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህም ሌብነትና ኮንትሮባንድን በመጸየፍ እውነተኛ የኢኮኖሚ አርበኛ መሆን ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አምራቾች በአገር ውስጥ የማምረት ተግባር ላይ ብቻ ተወስነው የሚቆዩበት ጊዜ አብቅቶ፣ አሁን ወደ አፍሪካ ሰፊ ገበያ የሚገቡበት ወቅት ላይ መሆኑንም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የገለጹት።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8769682

3. ቀልጣፋና ግልፅ የታክስ አስተዳደር አገልግሎት ለአምራቾች ማቅረብ አስፈላጊ ነው – የገቢዎች ሚኒስቴር

ኤፍ ኤም ሲ፡ግንቦት 3፣ 2018

ቀልጣፋና ግልፅ የታክስ አስተዳደር አገልግሎት ለኢንዱስትሪ አምራቾች ማቅረብ አስፈላጊ ነው አለ የገቢዎች ሚኒስቴር።

ሚኒስቴሩ በዛሬው ዕለት ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ቢሮ በኢስተርን ኢንዱስትሪያል ፓርክ በመክፈት ስራ አስጀምሯል።

የገቢዎች ሚኒስትር ዴኤታ መስከረም ደበበ በዚህ ወቅት እንዳሉት፦ በተያዘው በጀት ዓመት 13 ቢሊየን ዶላር የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ ተችሏል።

በዚህም በርካታ አምራቾች ገብተው ስራ ላይ መሰማራታቸውን ገልጸው፦ ቀልጣፋና ግልፅ የታክስ አስተዳደር አገልግሎት ለኢንዱስትሪ አምራቾች ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን በመገምገም ሚኒስቴሩ ቢሮውን በኢንዱስትሪያል ፓርክ ውስጥ መክፈቱን ተናግረዋል።

የቁጥጥር ዘርፉን ለማስጨነቅ ሳይሆን የግብር ስርዓቱን ድጋፍና ክትትል እንዲሁም አገልግሎት ለማቅረብ የታሰበ መሆኑን አንስተዋል።

ግብር ከፋዩን ከመቅረብ በዘለለ ማስተማር ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ይህንን ታሳቢ በማድግ ቢሮው መክፈቱንም አስረድተዋል።

ቢሮው የህግ ግንዛቤን በመፍጠር ባለሃብቱ በአግባቡ እንዲሰራ ለማገዝ ይረዳልም ነው ያሉት።

https://www.fanamc.com/archives/314610

4. የኢንዱስትሪ ዘርፍ አቅምን የገለጠው ኢትዮጵያ ታምርት

ኤፍ .ኤ.ም .ሲ፡ ሚያዚያ 25፣ 2018

ኢትዮጵያ የብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ ፖሊሲን በመከተል ሀገራዊ ብልጽግናን እውን ለማድረግ በአስደናቂ ጉዞ ላይ ትገኛለች፡፡ ከዚህ ቀደም በግብርና ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የነበረውን የኢኮኖሚ ትኩረት በማስፋት በኢንዱስትሪ፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም እና በአይቲ ዘርፎች ያለውን ዕምቅ አቅም በመጠቀም የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ ውጤት ተመዝግቧል። በዚህ ረገድ በተለይም ከውጭ የሚገባውን ምርት በመቀነስ እና ወደ ውጭ የሚላክ ምርትን በማሳደግ የተጀመረው የአምራች ኢንዱስትሪው ንቅናቄ በአብነት ይጠቀሳል።

በዚህም ኢትዮጵያ ከውጭ ከሚገቡ የኢንዱስትሪ ምርቶች ጥገኝነት ተላቅቃ ራስን በመቻል ብቻ ሳትገደብ ለውጭ ገበያ በማቅረብ በአስደናቂ የኢንዱስትሪ ሽግግር ሂደት ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት የተጀመረው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ስር ነቀል ለውጥ በማምጣት ረገድ ገና ከጅምሩ ተጨባጭ ውጤቶች የተመዘገቡበት ሆኗል፡፡ በንቅናቄው አማካኝነት ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተዘጉ ፋብሪካዎችን ዳግም ሥራ በማስጀመር፣ ምርታማነትን በማሳደግና በስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ገቢ ምርቶችን በመተካት በቢሊየን ዶላር የሚገመት የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል፡፡ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው በተለይም በተኪ ምርቶች ረገድ ባለፉት 9 ወራት ብቻ 4 ነጥብ 85 ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ ምርት በሀገር ውስጥ ተመርተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት ብቻ ሳይሆን ምርታማነትን በማሳደግ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ርዕይን ያነገበ ነው፡፡

https://www.fanamc.com/archives/314105

5.Officials Brief Development Partners on WTO Progress, AfCFTA Developments

The Reporter: May 12, 2026

Senior officials from the Finance and Trade ministries met today with members of the Development Partners Group (DPG) to deliberate on Ethiopia's accession to the World Trade Organization (WTO) and the implementation of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA).

Semereta Sewasew, a state minister of Finance, told the representatives of DPG agencies, which include the World Bank, IMF, UNDP, and the German, Korean, and Japanese development agencies as well as several diplomatic missions, that WTO accession remains a priority for the Ethiopian government.

Kassahun Gofe, minister of Trade and Regional Integration, highlighted the "sustained momentum" of the WTO accession process, which has dragged on for more than two decades. He noted vastly improved progress over the past year, which saw three WTO Working Party meetings.

Last month, the Ministry disclosed it would likely roll back the ban on the import of fuel-powered vehicles as part of its efforts to join the WTO. Officials, however, said they would introduce other measures aimed at discouraging the import of non-electric vehicles.

During this week's meeting, officials noted that Ethiopia has officially launched shipments under the AfCFTA framework in October 2025, opening trade channels to Kenya, Somalia, and South Africa.

https://www.thereporterethiopia.com/50674/

6. **Ethiopian Airlines Receives Best Airline in Africa 2026 APEX Passenger Choice Award**

ENA: 4 May 2026

Ethiopian Airlines has received Best Airline in Africa 2026 APEX Passenger Choice Awards, a recognition that reflects the confidence and loyalty of passengers who continue to choose the airline across its global network. The award highlights Ethiopian Airlines' steady focus on delivering a smooth, comfortable, and dependable travel experience, from the moment passengers book their flights to the time they reach their destinations.
Consistently strong service, onboard comfort, and operational reliability have all played a role in meeting the changing expectations of today's travelers.
https://www.ena.et/web/eng/w/eng_8772325

7.Minister: "Made In #Ethiopia" Expo Projected To Attract 150,000 Visitors And Generate Over 5 Billion Birr In Trade Deals

FMC: May 2, 2026

Ethiopia's efforts to strengthen its manufacturing sector are gaining momentum, with the government positioning the upcoming 4th Made in Ethiopia Expo as a key platform for industrial growth, trade expansion, and innovation, according to the country's industry ministry.

Briefing the media ahead of this year's expo, Industry Minister Melaku Alebel said the "Made in Ethiopia" initiative is already improving the competitiveness of local manufacturers by enhancing productivity. He added that the initiative is also addressing structural bottlenecks and expanding market access through coordinated policy support and targeted interventions.

Officials said the event is expected to attract more than 150,000 local and international visitors, bringing together manufacturers, investors, policymakers, and innovators in a large-scale exhibition of Ethiopia's industrial capacity. They further indicated that the expo is projected to facilitate over 850 trade agreements valued at more than 5 billion birr, underscoring its role as both a commercial platform and a policy-driven instrument for industrial expansion.

Beyond showcasing locally produced goods, the event is designed to promote innovation, technology transfer, and knowledge sharing across different sectors. Startups will be provided dedicated space to engage with established firms, with opportunities to scale their ideas into commercial ventures.

https://www.fanamc.com/english/minister-made-in-ethiopia-expo-projected-to-attract-150000-visitors-and-generate-over-5-billion-birr-in-trade-deals/

8. Ethiopia defers Eurobond payment to next fiscal year

Capital: May 12, 2026 : The Ethiopian government has officially announced the deferral of its Eurobond debt payment obligations to the next fiscal year. This decision is framed as a core component of a broad macroeconomic reform aimed at shifting the country's debt distress rating from "High Risk" to "Moderate Risk." According to the Ministry of Finance (MoF) , although a partial payment for the $1 billion Eurobond was initially anticipated for the 2025/26 fiscal year, the payment has now been rescheduled.**https://capitalethiopia.com/2026/05/12/ethiopia-defers-eurobond-payment-to-next-fiscal-year/**